Amharic

# ጠቃሚ መረጃ

## እድሜያቸው ከአሥራ ስምንት አመት በታች የሆኑ ልጆች ካሏችሁ

የኦንታርዮ የልጆች ድጎማ ፕሮግራም (ኦሲቢ) አነስተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች ልጆቻቸውን ለማሳደግ እንዲረዳቸው የተቀየሰ አዲስ ፕሮግራም ነው።

ከ አሥራ ስምንት አመት በታች የሆኑ ልጆች የአሏቸው የኦንታርዮ ነዋሪዎች በገቢያቸው መጠን ከጁላይ 2008 ጀምሮ የልጆች ድጎማ ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

ለዚህ የብቃት መስፈርቶቹም፣

- ከአሥራ ስምንት አመት በታች የሆነ ልጅ ያላቸው
- ነዋሪነታቸው ኦንታርዮ የሆነ
- የገቢ ቀረጣቸውን የከፈሉ
- ለካናዳ የልጆች ቀረጥ ጥቅም የተመዘገቡ

**ይህ በኦንታርዮ የሰራተኛ ጥቅም ላይ የሚኖረው ተጽእኖ ምን ይመስላል?**

- ከ ኦውገስት 1/2008 ጀምሮ ከአሥራ ስምንት አመት በታች ለሆኑ ልጆችዎ የክረምት (ዊንተር) ልብስና ወደ ትምህርት ቤት ለመመለስ የሚደረግ ድጎማ አይሰጣቸውም። በምትኩ ከላይ የተጠቀሱት ጥቅማ ጥቅሞች በኦንታርዮ የልጆች ድጎማ ፕሮግራም ወርሀዊ ክፍያ ውስጥ የሚካተቱ ይሆናል።
- የኦንታርዮ ሰራተኛ ድጎማ ለመጠለያ፣ ለጤናና ለጥርስ ሕክምና ለልጆች የሚሰጠውን ጥቅም/ድጎማ መስጠቱን ይቀጥላል
- ከ ኦውገስት 2008 ጀምሮ ብሄራዊ የልጆች ድጎማ ክፍያ ከ ኦንታርዮ ሰራተኛ ክፍያ ላይ አይቀነስም።

**የ ኦንታርዮ የልጆች ድጎማ/ጥቅምን በሚመለከት ተጨማሪ መረጃ ይፈልጋሉ?**

ሪቬንዩ ካናዳ 1-888-789-4199, TTY 1-800-387-5559 ደውለው ይጠይቁ ወይም ይህን ድህረ ገጽ ይመልከቱ www.OntarioChildBenefit.ca